
# <u>እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2019 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

ባለፉት የኤፕሪል አስር ቀናት ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ካለፉት አስር ቀናት በተሻለ መለኩ ተጠናክሮ ተስተውሏል፡፡ በተለይም በመካከለኛው፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ይበልጥ ከመጠናከራቸዉ ጋር በተያያዘ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንዲኖር አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡ ይሁንና ግን በማዳካስካር አካባቢ በተከታታይ በተፈጠረው ዝቅተኛ የአየር ግፊት ምክንያት በዚህ ወቅት በዋናነት ዝናብ በሚጠበቅባቸው የቦረናና ጉጂ እንዲሁም የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከነበራቸው የደመና ሽፋን በስተቀር የዝናብ እጥረት እንደነበር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በማሻ 98፣ 30.4 እና 40.2፣ በጭራ 42.7፣ በጋቲራ 32.2፣ በአይራ 37.4፣ በአርጆ 36.2 እና 32፣ በተርጫ 34.1፣ በጎሬ 31.4፣ በአልጌ 3.2፣ በሆሳዕና 47.2 እና 32 በጋምቤላ 52.0፣ በሻምቡ 32.1፣ በቡሬ 48.6፣ በደምቢዶሎ 66.5 እና በቡርጅ 31.3 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም የምስራቅና ደቡብ ትግራይ፤ ከሰሜን ጎንደር ምዕራባዊው ክፍል በስተቀር ሁሉምየአማራ ዞኖች፤ ከአፋር ዞን 1፣ 2፣ 3ና 5፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ የጋምቤላ፤ ከመተከል ምዕራባዊው ክፍል በስተቀር ሁሉም የቤንሻንጉል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ ሀረርጌ፣ አርሲና ባሌ እንዲሁም የሰሜን ሸዋ ክልል 4፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፣ እንዲሁም ከሶማሌ ደገሀቡርና ቀብሪደሀር ከ5-230 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ የተመዘገበባቸዉ ሲሆን፤ በዝናብ ቀናት ረገድም ከ2-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸው። በሌላ በኩል ከኦሮሚያ አብዛኛው ቦረናናጉጂ፣ ምስራቅ ሀረርጌ፣ አብዛኛው ሶማሌ እንዲሁም በምዕራብ ጫፍ የሚገኙ የትግራይ፣ የአማራና የቤንሻንጉል-ጉሙዝ አካባቢዎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል(ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር የምስራቅና ደቡብ ትግራይ፤ ከምዕራብ አማራ በስተቀር ሁሉም የአማራ ዞኖች፤ የአፋር ምዕራባዊው ክፍል፤ ጋምቤላ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሀዲያና ጉራጌ፣ የከፋ ዞን፣ የቤንች ማጂ፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሀረርጌ፣ የሰሜን ሸዋ ክልል 4 እና ያቤሎ እንዲሁም አዲስ አበባ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛው ያነሰ ዝናብ የነበራቸው በመሆኑ በአመዛኙ ፀሐያማና ሞቃታማ ሆነው ሰንበተዋል (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1ከኤፕሪል 11እስከ 20/2019ድረስየነበረውየዝናብመጠንበሚ.ሜ



ካርታ 2እ.ኤ.አከኤፕሪል 11እስከ 20/2019ድረስዝናብየዘነበባቸውቀናትብዛት




ካርታ3እ.ኤ.አከኤፕሪል 11እስከ 20/2019
ድረስየነበረውየዝናብመጠንከመደበኛውጋርበመቶኛሲነፃፀር



# <u>እ.ኤ.አ ከኤፐሪል 11-20/ 2019 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
# <u>በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ባሳለፍነው የኤፐሪል ሁለተኛዉ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የበልግ ሰብል አብቃይና የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአንፃራዊ መልኩ ከባለፉት አስር ቀናት የተሻለ የእርጥበት ይዘት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ አካባቢዎችም ከባድ ዝናብ እንደነበራቸው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰበሰቡ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ በአንዳንድ አካባቢዎች ተስተውሎ የነበረውን የእርጥበት እጥረት ያረገበ ከመሆኑም በላይ አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ስብሎች እና ቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አኳያ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተለይም ከኤፐሪል ጀምሮ ለሚዘሩ የረጅም ጊዜ ሰብሎች ማሳን ለማዘጋጀትም ሆነ ዘር ለመዝራት ጠቀሜታው የጎላ ነዉ፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የተመዘገበው ከባድ ዝናብ ለጎርፍ መከሰት ምቹ ሁኔታ የነበረዉ ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተወሰነ መልኩ በንብረትና በተወሰኑ ሰብሎች ላይ ጉዳት አስከትሏል፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው በአዎንታዊ መልኩ ውኃን ለመሰብሰብና ለማጠራቀም ጥሩ ሁኔታ የፈጠረ ነበር፡፡ በሌላ መልኩ በዚህ ወቅት እርጥበታማ ሁኔታ በሚጠበቅባቸው የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ኦሮሚያ አካባቢዎች በደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ስር ነበሩ፡፡ በነዚህ አካባቢዎች ላይ በተከታታይ እየተስተዋለ ያለው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የነበረውን የእርጥበት እጥረት ከማባባስ ጋር ተያይዞ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አከኤፐሪል 11 እስከ 20/2019 ድረስየነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# <u>እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11-20/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>
# <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

እ.ኤ.አ 11-20ኤፕሪል 2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው ተፋሰሶች በአብዛኛዉ ባሮ አኮቦናአፋር ደናክል፣መካከለኛዉ ዋቢ ሸበሌ፣ የላይኛውና የመካከለኛዉ ስምጥ ሸለቆ፣የታችኛዉ ገናሌ ዳዋ፣የአባይ ደቡባዊ እና ምስራቃዊው ክፍል፣የላይኛዉ አዋሽ፣ እንዲሁም የላይኛዉና መካከለኛዉ ኦሞ ጊቤና ተከዜ ተፋሰሶች ናቸው። በሌላ በኩል መጠነኛ እርጥበት የነበራቸው ተፋሰሶች ደግሞ የታችኛው ኦሞ ጊቤ፣በጥቂት የታችኛዉ ስምጥ ሸለቆ፣ አብዛኛው ዋቢ ሸበሌ፣ የመካከለኛው አዋሽ፣ የመካከኛዉ እና የላይኛዉ ገናሌ ዳዋ፣ የታችኛዉ አፋር ደናክልና ኦሞጊቤ፣ የአባይ መካከለኛዉና ደቡባዊው ክፍል እና የላይኛውና መካከለኛዉ ዋቢ ሸበሌቦታዎች ሲሆኑ፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደርቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏለል (ካርታ 5)።

ካርታ 5. እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 11 እስከ 20/2019ድረስበተፋሰሶች ላይ
የነበረው የእርጥበት መጠን



# <u>እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2019 የሚኖረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ በልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ እስከ አፕሪል የመጨረሻዎቹ አሥር ቀናት ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተጨማሪም ከአመቺ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶችመጠናከር ጋር ተያይዞ ወቅታዊው ዝናብ ቀስ በቀስ ወደ ምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ የሚሄድበት ጊዜ ነው ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናትዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሞላ ጎደል ተጠናክረው እንደሚቀጥሉና በተለይም የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን እንደሚገባ ከሚጠበቀው እርጥበት አዘል አየር ጋር ተያይዞ የተሻለ የደመናና የዝናብ ሥርጭት በደቡባዊው አጋማሽ እና በምዕራባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እንደሚቀጥል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በመጠን ረገድም በአብዛኛው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖርና በአንዳንድ ሥፍራዎችም ላይ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም እንደሚችል ይጠበቃል::

በአጠቃላይ በሚቀጥሉትአሥር ቀናት<u>ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ የሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብና የምሥራቅ ሐረርጌ፣ አርሲና ቦሌ፤ ከሶማሌ ክልል የፋፈን እና የሲቲ ዞኖች ሰሜናዊው ክፍል፤ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋና ሀረሪ፤ ጋምቤላ፤ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልልዞኖች፤ ከአማራ ክልል የዋግህምራ፤ የደቡብና የሰሜን ወሎ ዞኖች፤ ከትግራይ ክልል የመካከለኛው፤ የምሥራቅና የደቡብ ዞኖች፤ የአፋር ዞን 1፣3 እና 5 መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ አልፎ አልፎ ከሚኖሩ ጠንካራ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ይኖራል። በተጨማሪም የምሥራቅ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ ጋምቤላ እንዲሁም ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ጥቂት የደቡብ ሶማሌ ዞኖች እንዲሁም ቦረናና ጉጂ በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።</u>

# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ሶስተኛዉ አስር ቀናት ከእርሻ እንቅስቃሴ አኳያ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች በስርጭትም ሆነ በመጠን ረገድ ጥሩ ዝናብ የሚያገኙበት እንዲሁም የመኸርወቅት የረጅም ጊዜ ሰብል አብቃዮች የማሳ ዝግጅትና የዘር እርሻ እንቅስቃሴ የሚጀምሩበትና ዋነኛየዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ አርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ከፍተኛ ዝናብየሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡

በመጪዎቹ የኤፕሪል ሶስተኛው አሥር ቀናት ከላይ በትንበያዉ እንደተገለፀዉ በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስፋፋ እርጥበት ሊቀጥል እንደሚችልና በተለይም በደቡባዊው አጋማሽ እና በምዕራባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይእንደሚቀጥልየትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህም ሁኔታ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙት የበልግ ሰብሎች ጠቀሜታ ሲኖረው ለቋሚ ተክሎች የውሀ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም ለአርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በተጨማሪም ውኃ አጠር የሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚገኘውን የዝናብ ውኃ ለማቆርና ለማጠራቀም የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ስለሚጠበቅ አርሶ አደሮች፡ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ የሚጠበቀው ከመደበኛው በላይ የሆነ የእርጥበት መጠን በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች በተወሰነ መልኩ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረዉ ቢችልም፤ በቀጣይነት ለሚኖረው ለአዝዕርቱም ሆነ ለግጦሽ ሳር የውሃ አቅርቦት ጠቀሜታ ሰለሚኖረው የተለያዩ የውሃ ማቆር ስራዎችን በማከናወን ዕጥረት በሚገጥምበት ጊዜ በአንዳንድ ማሣዎች ላይ ዉሃዉን ለመጠቀም ይረዳል። በሌላ በኩልየሚጠበቀዉ ከባድ ዝናብ በተለያዩ የዕድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረዉ ስለሚችል የሚመለከተዉ አካል አስፈላጊዉን ጥንቃቄ እንዲያደርግይመከራል።

# <u>እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 21-30/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ የዝናቡ ስርጭትና መጠን በተሻለ መልኩ እንደሚስተዋል የትንበያ መረጃይ ጠቁማል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የአባይ ደቡባዊውና ምስራቃዊው ክፍል፣ በአብዛኛው ስምጥሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ኦሞ ጊቤና ተከዜ የላይኛውና የታችኛዉ አዋሽ፣ የላይኛው ዋቢሸበሌና ገናሌ ዳዋ እንዲሁም የላይኛው አዋሳኝ አፋር ደናከል ተፋሰሶች የተሻለ የርጥበት መጠን እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ይኸም ሁኔታ በአጠቃላይ ለውሃ ሀብት ጥሩ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡ ፡በመሆኑም ይህ ሁኔታ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ስለሆነ አስፈላጊ ጥንቃቄ እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡ እንዲሁም በጥቂት የታችዉና የመካከለኛ አባይ፣ የላይኛው ኦጋዴን እንዲሁም የዋቤሸበሌ ደበባዊው ክፍል መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት ተፋሰሶች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም ያለውን የውሃ ሃብት በአግባቡ መያዝና የውሃ እጥረት የሚታይባቸው ተፋሰሶች ላይ የሚገኘውን ዝናብ ለመጠቀም መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡